ቀን

የ ጋብቻ ውል

ክፍል አንድ የጋብቻ ውል አድራጊዎች ስም

1. አድራሻ ከተማ ----- ቀበሌ ------ የቤት. ቁ

2. አድራሻ ከተማ ----- ቀበሌ ------ የቤት. ቁ

ክፍል ሁለት ጠቅላላ ሁኔታ

1. የጋብቻውን ስነስርአት የፈፀምነው እንደ ባህላችን መሰረት በ አዋጅ ቁጥር 79/2003 አንቀፅ 11 መሰረት የአካባቢው ሽማግሌዎች ባሉበት በሁለታችንም ወገን ቤተሰቦቻችንን በማስፈቀድ ነው።

2. እኛ ተጋቢዎች ተዋደን እና ተፈቃቅደን ፡ በመግባባት በሀገራችን ባህል መሰረት ፡ ቤተሰቦች እና ምስክሮች በተገኙበት ይህንን የ ጋብቻ ውል ስንፈፅም በ አዋጅ ቁጥር 79/2003 ከ አንቀፅ 17 እስከ 20 ያሉትን የቤተሰብ ህጉን ድንጋጌዎች በማክበር ነው።

ክፍል ሶስት ስለ ንብረት ባለቤትነት እና አስተዳደር

3. ሁለታችንም ተጋቢዎች ከ ትዳር በፊት በግላችን ያፈራናቸው ንብረቶች የየግላችን ሆነው በ ትዳሩ ውስጥ እንዲቀጥሉ በ አዋጅ ቁጥር 79/2003 አንቀፅ 68 መሰረት ተስማምተናል ። ስለሆነም በ ባል የግል ንብረትነት ተመዝግበው የሚገኙትን ንብረቶች ማለትም በ ----------ከተማ -------ቀበሌ -----የቤት ቁጥር ----ተመዝግቦ የሚገኘው የመኖሪያ ቤት እና በ ስም ተመዝግቦ የሚገኘው ተሽከርካሪ የ ሰሌዳ ቁጥር ------ -----የባል የግል ንብረት ሆኖ በትዳር ዘመኑ እንዲቀጥል በጋራ ተስማምተናል።
4. የ ግል ንብረት አስተዳደርን በተመለከተ የ ንብረቱ ባለቤት ተጋቢ የግሉን ንብረት ያስተዳድራል ፡ የንብረቱን ገቢዎችም እራሱ ይሰበስባል ። እንደ አስፈላጊነቱ ውክልና ለ ትዳር አጋር ሊሰጥ ይችላል ።
5. በትዳር ውስጥ የምናፈራቸው ንብረቶች የጋራ ሆነው ይቀጥላሉ ፡ በጋራ እናስተዳድራቸዋለን ።

ክፍል አራት የተጋቢዎች ሀላፊነት

6. እኛ ተጋቢዎች እርስ በርሳችን መቻቻል እና ለመረዳዳት አለብን

7. የቤተሰቡን አስተዳደር በተመለተ የጋራ ሀላፊነቶች አሉብን ፡ በጠቅላላው በ አዋጅ ቁጥር 79/2003 አንቀፅ 60. 61 እና 62 መሰረት ለ ተዳራችን መስመር ሁለታችንም የበኩላችንን አስተዋፅኦ ማበርከት አለብን ።

ይህ የጋብቻ ውል ከተፈራረምንበት ቀን ጀምሮ ፡ በፍትሀ-ብሄር ህግ ቁጥር 1731፣ 1732፤ 2005 እና አዋጅ ቁጥር 79/2003 አንቀፅ 11 መሰረት በመካከላችን የፀና ነው ።

ይህ የጋብቻ ውል ሲደረግ የነበሩ ምስክሮች

በ ባል ወገን

1. ስም ፊርማ

2. ስም ፊርማ

በሚስት ወገን

1. ስም ፊርማ

2. ስም ፊርማ